Washington State Health Care Authority

# Medicare እና Apple Health Classic Medicaid

## በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

### በMedicare እና በApple Health Classic Medicaid መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ሁለቱም ፕሮገራሞች ዕድሜያቸው 65 የሞላው ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑትና ማየት የተሳናቸው ወይም የአካል ጉዳተኝነት ላለባቸው ወይም የረጅም ጊዜ አገልግሎቶችና ድጋፎች ለሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች ናቸው። የፕሮግራም ልዩነት የሚያካትተው:

- Medicare በማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር (SSA) የሚመራ የፌደራል ኢንሹራንስ ፕሮገራም ሲሆን የገቢ ገደቦች የለውም።
- Apple Health Classic Medicaid በጤና እንክብካቤ ባለስልጣን (HCA) የሚተዳደር ሲሆን ብቁ የመሆን መስፈርትና ምዝገባው በማህበራውና ጤና አገልግሎቶች መምሪያ (DSHS) በኩል ነው። ብቁ የመሆን መስፈርት በገቢ፥ በሀብት፥ በመኖሪያ፥ እና በዜግነት ወይም በስደተኝነት በመሳሰሉት ሁኔታዎች ላይ ይመሠረታል።

### ለApple Health Classic Medicaid ብቁ ለመሆን ለMedicare ማመልከት አለብኝ?

አይደለም፥ ለApple Health Classic Medicaid ከማመልከትዎ በፊት ለMedicare ማመልከት የለቦትም። ከ65 ዕድሜ በታች ሆነው የአካል ጉዳተኝነት ካለቦትና Apple Health እየተቀበሉ ከሆነም ለMedicare ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

### ለMedicare ማመልከቻዬ እንዴት እገዛ ማግኘት እችላለሁ?

SSA ጋር በመደውል ወይም የዋሽንግተን ስቴት የጤና ኢንሹራንስ ጥቅማጥቅሞች አማካሪዎች (SHIBA)ን በማነጋገር እገዛ ሊያገኙ ይችላሉ። SHIBA ለMedicareና ለሌላ የጤና እንክብካቤ ድጋፍ ነፃና ምስጥራዊነቱ የተጠበቀ አገልግሎቶችን ያቀርባል።

- SSA:
  - **ስልክ ቁጥር፦** 1-800-772-1213 (TTY: 1-800-325-0778)
  - **ኦንላይን:** ssa.gov
- SHIBA:
  - **ስልክ ቁጥር፦** 1-800-562-6900
  - **በአካል፡** insurance.wa.gov/find-local-shiba-office
  - **የቋንቋ ሊንክ አገልግሎቶች**: insurance.wa.gov/language-link-services

### በተመሳሳይ ጊዜ Medicare እና Apple Health Classic Medicaid ማግኘት እችላለሁ?

አዎ፥ ሁለቱንም ማለትም Medicareን እና Apple Health Classic Medicaidን ማግኘት ጥቅሞች አሉት። Apple Health Medicare የማይሸፍነው እንደ እነ ተቀናሾች፥ በጋራ መክፈል፥ የመስሚያ ድጋፎችን እና የጥርስ ሕክምና አገልግሎቶች ያሉትን ለመሸፈን ይረዳል። Apple Health Classic Medicaid የሜድኬድ ፕሪምዬሞችዎን ለመሸፈን የሚያግዝ የMedicare ቁጠባዎች ፕሮግራሞችንም (MSP) አለው።

Medicaid Programs Division - Office of Medicaid eligibility Policy
Source: cms.gov/MLNMattersArticles/Downloads/SE1128.pdf
May 12, 2022

HCA 19-0080 Amharic

## የMedicare ቁጠባዎች ፕሮግራሞች ምንድን ናቸው?

የMedicare ቁጠባዎች ፕሮግራሞች ግለሰቦች የMedicare ፕሪምዬሞቻቸውን እንድከፍሉ ያግዛቸዋል። ይህ ክፍል ሀ እና ክፍል ለ ፕሪምዬሞችንና ምናልባትም እንደ የጋራ ኢንሹራንና ተቀናሾች ያሉት ሌሎች ከMedicare ጋር የሚገናኙ ወጪዎችን የሚያካትት ነው።

# ግብዓቶች

### Medicare

- የኔ ማህበራዊ ዋስትና | SSA
- የMedicare ጥቅማጥቀሞች | SSA
- ፎርሞች፣ እገዛ እና ግብአቶች | Medicare
- ተጨማሪ የእገዛ ፕሮግራም: Medicare's Part D Low-Income Subsidy (medicareinteractive.org)

### Medicare የቁጠባ ፕሮግራሞች:

- የMedicare የቁጠባ ፕሮግራሞች ብሮሸር | HCA
- የMedicare የቁጠባ ፕሮግራሞች | HCA

### Apple Health Classic Medicaid እና/ወይም Medicare ቁጠባዎች ፕሮግራም ያመልክቱ፡

- DSHS ኦንላይን ማመልከቻ: ዋሽንግተን ኮነክሽን | DSHS
- የወረቀት ማመልከቻ ለMedicare ቁጠባዎች ፕሮግራም ማመልከቻ | HCA